# በኮቪድ -19 (ኮሮና ቫይረስ) ወቅት የታክስ

# ይግባኝ ኮሚሽን የዳኝነት ስራውን በአግባቡ ለመፈፀም እንዲችል የተዘጋጀ

# የአሠራር ማኑዋል ቁጥር 01/2012

የኮሮና ቫይረስ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሀገር ሊጠፋ ይችላል ተብሎ ስለማይገመት፤

የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የዳኝነት ውሳኔ የሚያስተላልፍ አካል እንደመሆኑ መጠን ፍትህ በወቅቱ ተደራሽ እንዲሆን መደረግ ያለበት በመሆኑ፤

የበሽታውን ባህሪ ከግምት ውስጥ በማስገባት የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ይኽን የአሰራር ማኑዋል አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ማኑዋል "የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በኮሮና ቫይረስ ወቅት የዳኝነት ስራውን በአግባቡ ለመፈጸም እንዲችል የሚረዳ የአሠራር ማኑዋል ቁጥር 01/ 2012 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   1. "ኮሚሽን" ማለት እንደ አግባብነቱ ሌላ ስም ካልተሰጠው በስተቀር የፌዴራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ማለት ነው፡፡
   2. "ዳኝነት" ማለት የፌዴራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በህግ በተሠጠው ተግባርና ኃላፊነት መሠረት የሚሠጠው ዳኝነት ነው፡፡
   3. "ሬጅስትራር" ማለት የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ሬጅስትራር ማለት ነው፡፡
   4. "ይግባኝ ባይ" ማለት ለኮሚሽኑ ይግባኝ የሚያቀርብ ሰው ነው፡፡
   5. "መልስ ሰጭ" ማለት ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም የጉምሩክ ኮሚሽን ነው፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Tax Appeal Commission